**መመሪያ ቁጥር ----/2016**

**ለደረቅ ወደብና ተርሚናል ልማት እና አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥን ለመወሰን የወጣ መመሪያ /ረቂቅ/**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነሐሴ 2011 ዓ.ም ባፀደቀው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሎጂስቲክስ ስትራቴጂ፣ በደረቅ ወደብ ልማት እና አገልግሎት ዘርፍ ለመሰማራት የሚያስችል የፈቃድ አሠጣጥ ሥርዓትን ማሻሻል እንደ አንድ የስትራቴጂ ማስፈፀሚያ ስልት በማድረግ እንደ አቅጣጫ ማስቀመጡ፤

በደረቅ ወደብ ልማት እና አገልግሎት ዘርፍ ላይ መሠማራት ለሚፈልጉ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሃብቶች የፍቃድ አሠጣጥ ሂደት ላይ የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥበትን ሥርዓት እና የምዘና ሂደት እንዲሁም ይህ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ መወሰን በማስፈለጉ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚያዝያ 29/2012 ባደረገው 20ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ባፀደቀው የሎጂስቲክስ ዘርፍ ፖሊሲ እና በኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር 474/2020 በአንቀጽ 6 መሠረት የደረቅ ወደብ ልማትና አገልግሎት ለግል ባለሃብቶች ክፍት እንዲሆን የተወሰነ በመሆኑ፤

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር በማሪታይም አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 አንቀፅ 18(ለ) በተሰጠው ሥልጣን ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "**ለደረቅ ወደብና ተርሚናል ልማት እና አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር ------/2016**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2 ትርጉም**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1. "**ሚኒስቴር**" ወይም "**ሚኒስትር**" ማለት የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
2. "**ባለሥልጣን**" ማለት በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/2007 መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን ነው፤
3. "**ኩባንያ**" ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሰረት የተቋቋመ አክሲዮን ማህበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ነው፤

4. **"ደረቅ ወደብ እና ተርሚናል"** ማለት በሀገር ውስጥ የሚገኝ፤ ከባህር ወደብ ወይም ወደቦች ጋር በትራንስፖርት መሰረተ ልማቶች የተገናኘ፤ የተለያዩ የወደብ መሳሪያዎች የተሟሉለት፤ ለገቢና ወጪ ዕቃዎች መነሻና መዳረሻ ሆኖ የሚያገለግል እንዲሁም የተለያዩ የሎጅስቲክስ አገልግሎቶች የሚሰጥበት የተከለለ እና በተቀጣጣሪ ተቋማት ቁጥጥር የሚደረግበት ሆኖ የሎጅስቲክስ ሃብን፣ የሎጅስቲክስ ፓርክን እና ልዩ ተርሚናልን የሚያጠቃልል ቦታ ነው፤

5. **"የሎጅስቲክስ ፓርክ"** ማለት ለኮንቴይነር ጭነት፣ ለጥቅል እቃ፣ ለተሽከርካሪዎች መነሻና መዳረሻ ሆኖ በውስጡ ዕቃ የመጫንና የማራገፍ፣ ዕቃ ወደ ኮንቴይነር የማስገባትና ከኮንቴይነር ማውጣት፣ ዕቃ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማንቀሳቀስ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመጋዘን አገልግሎት፣ ዕቃዎችን ከአንድ የማጓጓዣ ዓይነት ወደ ሌላ የማጓጓዣ ዓይነት ማዛወር ፣የሎጅስቲክስ መገናኛ እና መረጃ አገልግሎት፣ ዕቃዎችን ማሸግ፣ዕቃዎችን የመገጣጠም አገልግሎት፣የኮንቴይነር እና የዕቃ ማጠን አገልግሎት፣የኮንቴይነር ጽዳትና ጥገና፣ የማማከር እና የስልጠና አገልግሎት፣ የባንክና የኢንሹራንስ አገልግሎት፣ የጉምሩክ አገልግሎት ፣የዕቃዎች ተስማሚነትና ምዘና አገልግሎት፣ የዕቃ / የጉምሩክ አስተላላፊነት አገልግሎት፣ የሎጅስቲክስ ማሽነሪዎች ኪራይ፣ የመርከብ ውክልና አገልግሎት፣ የተሽከርካሪ ምርመራ እና የጥገና አገልግሎት ፣ የምግብ ቤትና ካፌ አገልግሎት ፣ የክሊኒክ አገልግሎት ፣ ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው እሴት የሚጨምሩ የተለያዩ የሎጅስቲክስ አገልግሎቶች፣ የሎጅስቲክስ መገልገያ ምርቶችን ማምረት፣ ከከባድ መኪና ማጓጓዣ መሰረተ-ልማት ጋር የተገናኘ እና ዘመናዊ የወደብ መሳሪያዎች የተሟሉለት ሆኖ የተለያዩ የሎጅስቲክስ አገልግሎቶች በተለያዩ አከናዋኞች የሚሰጥበት የተከለለ ቦታ ነው፤

6. **"የሎጅስቲክስ ሀብ"** ማለት በሎጅስቲክስ ፓርክ ውስጥ ከሚሰጡ የሎጅስቲክስ አገልግሎቶች በተጨማሪ የደረቅ ብትን ጭነት፤ ነጻ የንግድ ቀጠና ፣ የቀዝቃዛ መጋዘን አገልግሎት ፣ ተጨማሪ እሴት በመጨመር የተለያዩ ምርቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች፣ የተለያዩ የሎጅስቲክስ መገልገያ ምርቶችን እና ለዕቃዎች ማሸጊያ የሚሆኑ ቁሳቁሶች የሚመረቱበት፤ በባቡር እና በከባድ መኪና መጓጓዣ መሰረተ-ልማት የተገናኘ ፣ ዘመናዊ የወደብ መሳሪያዎች የተሟሉለት እና በተለያዩ አከናዋኞች የተለያዩ የሎጅስቲክስ አገልግሎቶች የሚሰጥበት የተከለለ ቦታ ነው፣

7. **"ልዩ ተርሚናል"** ማለት ለገቢና ወጪ ዕቃዎች በዋናነት አንድ ዓይነት የደረቅ ወደብና ተርሚናል አገልግሎት የሚሰጥበት የተከለለ ቦታ ሲሆን ይኸውም በተናጠል የኮንቴይነር ተርሚናል፣ የደረቅ ብትን ጭነት ተርሚናል፣ የጥቅል ዕቃ ተርሚናል፣ የተሽከርካሪ ተርሚናል ወይም ኢንተርሞዳል ተርሚናል ሊሆን ይችላል፤

8. **"የኮንቴይነር ተርሚናል"** ማለት ዕቃ የመጫንና የማራገፍ፤ የመጋዘን አገልግሎት፣ዕቃዎች ወደ ኮንቴይነር የማስገባት እና ከኮንቴይነር ማውጣት፣ ዕቃዎችን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማንቀሳቀስ ፣ የኮንቴይነር ጽዳትና ጥገና፣ የምድር ሚዛን አገልግሎት፣ የኮንቴይነር እና ዕቃዎችን የማጠን

አገልግሎት፣ የባንክ አገልግሎት ፣ የጉምሩክ አገልግሎት፣ የዕቃዎች ጥራት እና ተገቢነት ቁጥጥር ፣ የዕቃ / የጉምሩክ አስተላላፊነት አገልግሎት እና ተያያዥ አገልግሎቶች የሚሰጡበት የተከለለ ቦታ ነው፤

9. "**ደረቅ ብትን ጭነት ተርሚናል**" ማለት ዕቃ መጫንና ማራገፍ፣ የብትን ጭነት መቋጠር፣ ዕቃን ከአንድ የማጓጓዣ ዓይነት ወደ ሌላ የማጓጓዣ ዓይነት ማዛወር፣ የጉምሩክ አገልግሎት፣ የምድር ሚዛን አገልግሎት፣ የዕቃ / የጉምሩክ አስተላላፊነት አገልግሎት፣ የባንክ አገልግሎት እና ተያያዥ አገልግሎቶች የሚሰጥበት የተከለለ ቦታ ነው፤
10. "**የጥቅል ዕቃ ተርሚናል**" ማለት ዕቃ የመጫንና የማራገፍ፣ ዕቃዎችን የመገጣጠም አገልግሎት፣ የምድር ሚዛን አገልግሎት፣ ዕቃን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማንቀሳቀስ፣ የባንክ አገልግሎት፣ የጉምሩክ አገልግሎት ፣ የዕቃዎች ጥራት እና ተገቢነት ቁጥጥር ፣ የዕቃ / የጉምሩክ አስተላላፊነት አገልግሎት እና ተያያዥ አገልግሎቶች የሚሰጥበት የተከለለ ቦታ ነው፤
11. "**የተሽከርካሪ ተርሚናል**" ማለት ዕቃ የመጫንና የማራገፍ፣ ዕቃ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማንቀሳቀስ፣ የባንክ አገልግሎት ፣ የጉምሩክ አገልግሎት፣ የዕቃ / የጉምሩክ አስተላላፊነት አገልግሎት፣ የጥገና አገልግሎት እና ተያያዥ አገልግሎቶች የሚሰጥበት የተከለለ ቦታ ነው፤
12. "**ኢንተርሞዳል ተርሚናል**" ማለት ዕቃ የመጫንና የማራገፍ፣ ዕቃዎችን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የማንቀሳቀስ፣ ዕቃዎችን ከአንድ የማጓጓዣ ዓይነት ወደ ሌላ የማጓጓዣ ዓይነት ማዛወር ፣ የባንክ አገልግሎት፣ የጉምሩክ አገልግሎት፣ የጥገና አገልግሎት እና ተያያዥ አገልግሎቶች የሚሰጥበት የተከለለ ቦታ ነው፤
13. "**መልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ**" ማለት ማንኛውም ሰው በራሱ ወይም በእሱ ስም በሚሰራ ሌላ ሰው አማካይነት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ውል የተዋዋለ፣ ዋና ሆኖ የሚሰራ ወይም በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ክንውን የሚሳተፍ እና ስለ ውሉ አፈጻጸም ሃላፊ የሆነ ሰው ማለት ነው፤
14. "**ደረቅ ብትን ጭነት**" ማለት ያለመጠቅለያ በከፍተኛ መጠን የሚጓጓዝ አንድ ዓይነት ዕቃ ሲሆን ስንዴ ፣ ማዳበሪያ ፣ በቆሎ፣ ማሽላ ፣ክሊንከር ፣የድንጋይ ከሰል ፣ስኳር እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፤
15. "**ጥቅል ጭነት**" ማለት በተለያዩ የዕቃ መያዣዎች /ማስሪያዎች ማለትም በጆንያ ፣ በእስር ፣ በበርሜል ፣ በሳጥን እና በመሳሰሉት የሚጓጓዝ ዕቃን ያጠቃልላል፤
16. "**ኢንተርሞዳል ትራንስፖርት**" ማለት አንድን ዕቃ ከአንድ መነሻ ቦታ እስከ መድረሻ ቦታ ከአንድ ዓይነት በላይ የማጓጓዣ ዘዴዎችን በመጠቀም ዕቃን ማጓጓዝ ማለት ነዉ፤
17. "**መልቲሞዳል ትራንስፖርት**" ማለት በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 548/1999 የተሠጠውን ትርጓሜ ይይዛል፤

18. **“ዕቃ ተረካቢ”፣ “ዕቃ ላኪ”፣ “ርክክብ”፣”፣ “የትራንስፖርት አይነት”፣ “ዕቃ” ፣ “ኃላፊነት መውሰድ”፣ “ማስረከብ”**፣ የሚሉት ቃላትና ሐረጎች በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 548/2007 የተሠጣቸው ትርጓሜ ይኖራቸዋል፤
19. "**ታሪፍ**" ማለት የደረቅ ወደብና ተርሚናል አገልግሎት ሰጪው ለሚሰጠው አገልግሎት የሚጠይቀው ክፍያ ነው፤
20. "**የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት**" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት መስፈርቶችን አሟልቶ አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችለው ቁመና ላይ መሆኑን ለማረጋገጥ በባለስልጣኑ የሚሰጥ ማሥረጃ ነው፤
21. "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፡፡
22. "**በቅንጅት የሚደረግ ኢንቨስትመንት**" ማለት የሃገር ውስጥ ባለሃብት እና የውጭ ባለሃብት ወይም እንደውጭ ባለሃብት መቆጠር የፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ በውጭ አገር የሆነ ኢትዮጵያዊ ጋር በቅንጅት የሚደረግ ኢንቨስትመንት ነው፤

**አንቀጽ 3፡- <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ የደረቅ ጭነትን ብቻ ለማስተናገድ የሚሆኑ የደረቅ ወደብና ተርሚናል ለማልማትና አገልግሎት ለመስጠት በሚሰማራ ወይም አልምቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ በሚገኝ ማንኛውም አልሚ እና አገልግሎት ሰጪ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ</u>

**አንቀጽ 4፡- <u>ለምዝገባ የሚያበቃ መሰረታዊ መስፈርት</u>**

ማንኛውም ሰው የደረቅ ወደብና ተርሚናል ልማት ለማካሄድ የሚከተለውን ማሟላት ይኖርበታል፤

1. በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጠው የግል ድርጅት፣ አክሲዮን ማህበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፤ የቅንጅት ኢንቨስትመንት እና የመንግስት የልማት ድርጅት የደረቅ ወደብና ተርሚናል ልማትና አገልግሎት ለመስጠት የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ለባለስልጣኑ ማመልከት፤
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ህግ መሠረት የተቋቋመ የግል ድርጅት በደረቅ ወደብና ተርሚናል ልማትና አገልግሎት ዘርፍ መሰማራት የሚችለው ለልዩ ተርሚናል ብቻ ነው፡፡
3. የአዋጭነት ጥናት ለባለስልጣኑ ማቅረብ፤

4. የኩባንያው ወይም የቅንጅት ኢንቨስትመንት መመስረቻ ፅሁፍ፣ የመተዳዳሪያ ደንብ እና የውጭ አልሚ ከሆነ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አሟልቶ ማቅርብ፣
5. ይህ መመሪያ የሚጠይቀውን የመሬት ይዞታ መጠን ያሟላ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም ከ4 ዓመት ያላነሰ የኪራይ ውል ማቅረብ፣

**አንቀጽ 5፡- <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማስፈለጉ፣</u>**

ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት፡-

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ላይ የተደነገጉ የደረቅ ወደብና ተርሚናል ልማት ለማካሄድ የሚያስችሉ መሰረታዊ መስፈርቶችን አሟልቶ ሲገኝ በባለስልጣኑ ሊመዘገብ ይችላል፣
2. የደረቅ ወደብና ተርሚናል መሰረተ ልማት በባለስልጣኑ ወይም ባለስልጣኑ በሚሰይመው ድርጅት ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ሲያቀርብ እና የወደብ መሳሪያዎች ፣ የደህንነት እና የጥበቃ ሥርዓት፣ ተፈላጊ የሰው ሃይል በመስፈርቱ መሰረት ማሟላቱ ሲረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በባለስልጣኑ ይሰጣል፣

## ክፍል ሶስት

## የልዩ ተርሚናል ልማት እና የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች

**አንቀጽ 6፡- <u>የደረቅ ወደብና ተርሚናል ዓይነቶች</u>**

በዚህ መመሪያ መሰረት የደረቅ ወደብና ተርሚናል ዓይነቶች ልዩ ተርሚናል፣ የሎጅስቲክስ ፓርክ እና የሎጅስቲክስ ሀብ ናቸው፡፡

**አንቀጽ 7፡- <u>የልዩ ተርሚናል ዓይነቶች</u>**

በዚህ መመሪያ ልዩ ተርሚናል የተባሉት የሚከተሉትን ያካትታል፣

1. ኮንቴይነር ተርሚናል
2. የደረቅ ብትን ጭነት ተርሚናል
3. የጥቅል ዕቃ ተርሚናል
4. የተሽከርካሪ ተርሚናል እና
5. ኢንተርሞዳል ተርሚናል

ናቸው፡፡

**አንቀጽ 8፡- በሁሉም የደረቅ ወደብና ተርሚናሎች ውስጥ መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች**

ማንኛውም የደረቅ ወደብና ተርሚናል አልሚ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፣

1. በየተርሚናሉ የተሟላ ኦፐሬቲንግ ሲስተም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት የተዘረጋለት፣
2. የመብራት፣ የውሃ እና የኢንተርኔት እንዲሁም የመጠባበቂያ የኤሌክትሪክ ሃይልና የውሃ አቅርቦት መሰረተ ልማት መገንባት፣
3. የከባድ  እና የቀላል ተሽከርካሪዎች መተላለፊያ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ፣
4. ከደረቅ ወደብና ተርሚናሉ አጠቃላይ ቦታ ከ1 ፐርሰንት ያላነሰ የሚሆነውን የውስጥ ለውስጥ አካፋይ መንገድ ፣ የመንገድ ዳርቻ፣ አደባባዮችና የህንጻ ዙሪያ በአረንጓዴ ተክሎች የለማ፣
5. የፍሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ መሰረተ ልማት፣
6. ከአንድ ያላነሰ የባህር ወደብ ጋር በሚያገናኝ እና ከባድ ተሽከርካሪዎችን በሚያስተላልፍ ከዋና መንገድ ጋር የተገናኘ፣

**አንቀጽ 9፡- <u>የኮንቴይነር ተርሚናል የመሰረተልማት እና የመሳሪያዎች ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለማግኘት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>**

ማንኛውም ሰው የኮንቴይነር ተርሚናል የመሰረተ ልማትና የወደብ መሳሪያዎች ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ቢያንስ የሚከተለውን ማሟላት ይኖርበታል፤

1. ከሶስት ሜትር ከፍታ ያላነሰ በሽቦ አጥር ወይም በግንብ የታጠረና ደህንነቱ በተጠበቀ በትንሹ በአጠቃላይ 2.5 ሄክታር ቦታ ያለው ከዚህ ውስጥ 1.75 ሄክታር ቦታ ላይ በአስፋልት ኮንክሪት የተገነባ ተርሚናል ፣
2. ባለ 45 ቶን 2 ሪች ስታከር (ወይም 1 ባለ 45 ቶን ሪች ስታከር እና 1 ባለ 45 ቶን ሞባይል ክሬን) ፣ ባለ 40 ቶን 2 ተርሚናል ትራክተር ከነተሳቢው እና ባለ 3 - 10 ቶን 3 ፎርክ ሊፍት በባለቤትነት ወይም ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ 2 ፎርክሊፍት ቢያንስ በአራት አመት ኪራይ እና ሌሎቹን በባለቤትነት፣
3. እያንዳንዳቸው ቢያንስ በ0.1 ሄክታር ቦታ ላይ የተገነቡ ሶስት መጋዝኖች፣
4. ለተቆጣጣሪ እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሆን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደራጀ ቢሮ፣
5. የጥገና እና የኮንቴይነር እጥበት ማዕከል፣
6. አንድ ባለ 2000 ሊትር የእሳት አደጋ ተሽከርካሪ የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያዎች፣ በአደጋ ጊዜ መውጫ በር እና መሰብሰቢያ ቦታ፣
7. የጥበቃ ማማ እና የደህንነት መሳሪያዎች ፣ የነፍስ ወከፍ አደጋ መከላከያ መሳሪያዎች፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የደህንነት የመቆጣጠሪያ ማዕከል እና የዕቃ መፈተሻ ማሽን መትከያ ቦታ፣
8. የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ማዕከል፣

9. በተርሚናሉ የኦፐሬቲንግ ሲስተም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት፣

10. በአንድ ጊዜ ለ15 ከባድ ተሽከርካሪዎች ማቆሚያ የሚሆን በአስፋልት ኮንክሪት የተገነባ ቦታ፣

## አንቀጽ 10፡- <u>የኮንቴይነር ተርሚናል የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>

ማንኛውም ሰው የኮንቴይነር ተርሚናል የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተለውን ማሟላት ይኖርበታል፤

1. አንድ ከፍተኛ የስራ መሪ እና ከ22 ያላነሱ ባለሞያዎች ያሉት እና ባለሞያዎቹ በዕቃ አስተላላፊነት፣ በጉምሩክ አስተላላፊነት፣ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት፣ በመርከብ ውክልና ቢያንስ የአምስት ዓመት ልምድ ያላቸው መሆኑ፤ እና
2. ለሚሰጠው አገልግሎት የተዘጋጀ ታሪፍ ያለው መሆኑ፣

## አንቀጽ 11 ፡- <u>የደረቅ ብትን ጭነት ተርሚናል የመሰረተልማት እና የመሳሪያዎች ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>

ማንኛውም ሰው የደረቅ ብትን ጭነት ተርሚናል የመሰረተ ልማትና የመሳሪያዎች ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተለውን ማሟላት ይኖርበታል፤

1. ከሶስት ሜትር ከፍታ ያላነሰ በሽቦ አጥር ወይም በግንብ የታጠረና ደህንነቱ በተጠበቀ በትንሹ በአጠቃላይ 2 ሄክታር ቦታ ያለው እና ከዚህ ውስጥ 0.25 ሄክታር ቦታ ላይ በአስፋልት ኮንክሪት የተገነባ ተርሚናል፣
2. ሁለት የመቋጠሪያ መሳሪያ፣ ቢያንስ ባለ 5 ቶን 1 ሎደር እና ባለ 3 ቶን 2 ፎርክ ሊፍት በባለቤትነት፣
3. በአጠቃላይ ቢያንስ በ1 ሄክታር ላይ የተገነቡ ሶስት መጋዘኖች፣
4. ለተቆጣጣሪ እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሆን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደራጀ ቢሮ፣
5. የወደብ መሳሪያዎች የጥገና ማዕከል፣
6. የጥበቃ ማማ እና የደህንነት መሳሪያዎች ፣ የነፍስ ወከፍ አደጋ መከላከያ መሳሪያዎች፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የደህንነት የመቆጣጠሪያ ማዕከል እና የዕቃ መፈተሻ ማሽን መትከያ ቦታ፣
7. ቢያንስ አንድ ባለ 2000 ሊትር የእሳት አደጋ ተሽከርካሪ እና ሌሎች የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያዎች፣ በአደጋ ጊዜ መውጫ በር እና መሰብሰቢያ ቦታ፣
8. የምድር ሚዛን ፣
9. የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ማዕከል፣
10. በአንድ ጊዜ ለ20 ከባድ ተሽከርካሪዎች ማቆሚያ የሚሆን በአስፋልት የተገነባ ቦታ፣

**አንቀጽ 12፡- <u>የደረቅ ብትን ጭነት ተርሚናል የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>**

ማንኛውም ሰው የደረቅ ብትን ጭነት ተርሚናል የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተለውን ማሟላት ይኖርበታል፤

1. አንድ ከፍተኛ የሥራ መሪ እና ከ26 ያላነሱ ባለሞያዎች ያሉት እና ባለሞያዎቹ በዕቃ አስተላላፊነት፣ በጉምሩክ አስተላላፊነት፣ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት፣ በመርከብ ውክልና ቢያንስ የአምስት ዓመት ልምድ ያላቸው መሆኑ፤ እና
2. ለሚሰጠው አገልግሎት የተዘጋጀ ታሪፍ ያለው መሆኑ፣

**አንቀጽ 13፡- <u>የጥቅል ዕቃ ተርሚናል የመሰረተልማት እና የመሳሪያዎች ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>**

ማንኛውም ሰው የጥቅል ዕቃ ተርሚናል የመሰረተ ልማትና መሳሪያዎች ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተለውን ማሟላት ይኖርበታል፤

1. ከሶስት ሜትር ከፍታ ያላነሰ በሽቦ አጥር ወይም በግንብ የታጠረና ደህንነቱ በተጠበቀ በትንሹ 3 ሄክታር አጠቃላይ ቦታ እና ከዚህ ውስጥ 1 ሄክታሩ በአስፋልት ኮንክሪት እንዲሁም 1 ሄክታሩ ደግሞ በቀይ አፈር የተነጠፈ ተርሚናል ፣
2. ባለ 45 ቶን 1 ሞባይል ክሬን፣ ባለ 3 - 25 ቶን 4 ፎርክ ሊፍት በባለቤትነት ወይም ከዚህ ውስጥ 2 ፎርክ ሊፍት ቢያንስ በአራት ዓመት ኪራይ ሌሎች ቀሪዎቹን በባለቤትነት፣
3. እያንዳንዳቸው ቢያንስ በ0.1 ሄክታር ቦታ ላይ የተገነቡ ሶስት መጋዝኖች፣
4. ለተቆጣጣሪ እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሆን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደራጀ ቢሮ፣
5. የወደብ መሳሪያዎች የጥገና ማዕከል፣
6. የጥበቃ ማማ እና የደህንነት መሳሪያዎች ፣ የነፍስ ወከፍ አደጋ መከላከያ መሳሪያዎች እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የደህንነት መቆጣጠሪያ ማዕከል ፣
7. አንድ ባለ 2000 ሊትር የእሳት አደጋ ተሽከርካሪ እና ሌሎች የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያዎች ፣ በአደጋ ጊዜ መውጫ በር እና መሰብሰቢያ ቦታ፣
8. የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ማዕከል፣
9. በአንድ ጊዜ ለ15 ከባድ ተሽከርካሪዎች ማቆሚያ የሚሆን በአስፋልት የተገነባ ቦታ፣

**አንቀጽ 14፡- <u>የጥቅል ዕቃ ተርሚናል የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>**

ማንኛውም ሰው የጥቅል ዕቃ ተርሚናል የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተለውን ማሟላት ይኖርበታል፤

1. አንድ ከፍተኛ የሥራ መሪ  እና ከ22 ያላነሱ ባለሞያዎች ያሉት እና ባለሞያዎቹ በዕቃ አስተላላፊነት፣ በጉምሩክ አስተላላፊነት፣ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት፣ በመርከብ ውክልና ቢያንስ የአምስት ዓመት ልምድ ያላቸው መሆኑ፤ እና
2. ለሚሰጠው አገልግሎት የተዘጋጀ ታሪፍ ያለው መሆኑ፣

## አንቀጽ 15፡- <u>የተሽከርካሪ ተርሚናል  የመሰረተልማት እና የመሳሪያዎች ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>

ማንኛውም ሰው የተሽከርካሪ ተርሚናል የመሰረተልማትና መሳሪያዎች ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተለውን ማሟላት ይኖርበታል፤

1. ከሶስት ሜትር ከፍታ ያላነሰ በሽቦ አጥር ወይም በግንብ የታጠረና ደህንነቱ በተጠበቀ በአጠቃላይ 1.5 ሄክታር ቦታ ላይ 0.7 ሄክታር ቦታ የተሽከርካሪ ተርሚናል ያለው ከዚህ ውስጥ 0.1 ሄክታሩ በቀይ አፈር እንዲሁም 0.6 ሄክታሩ በአስፋልት ኮንክሪት የተገነባ ተርሚናል፣
2. ሁለት ፎርክ ሊፍት በባለቤትነት፣
3. እያንዳንዳቸው ቢያንስ በ0.1 ሄክታር ቦታ ላይ የተገነቡ ሶስት መጋዘኖች፣
4. የተሽከርካሪ እና የወደብ መሳሪያ  የጥገና ማዕከል፣
5. የጥበቃ ማማ  እና የደህንነት መሳሪያዎች ፣ የነፍስ ወከፍ አደጋ መከላከያ መሳሪያዎች እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የደህነነት መቆጣጠሪያ ማዕከል ፣
6. ቢያንስ አንድ ባለ 2000 ሊትር የእሳት አደጋ ተሽከርካሪ እና ሌሎች የእሳት አደጋ መከላከያ ቁሳቁሶች፣ በአደጋ ጊዜ መውጫ በር እና መሰብሰቢያ ቦታ፣
7. የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ማዕከል፣
8. ለተቆጣጣሪ እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሆን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደራጀ ቢሮ፣
9. ቢያንስ በአንድ ጊዜ ለ10 ከባድ ተሽከርካሪዎች ማቆሚያ የሚሆን በአስፋልት የተገነባ ቦታ፣

## አንቀጽ 16፡- <u>የተሽከርካሪ ተርሚናል የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>

ማንኛውም ሰው የተሽከርካሪ ተርሚናል የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተለውን ማሟላት ይኖርበታል፤

1. አንድ ከፍተኛ ሥራ መሪ እና ከ15 ያላነሱ ባለሞያዎች ያሉት እና ባለሞያዎቹ በዕቃ አስተላላፊነት፣ በጉምሩክ አስተላላፊነት፣ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት፣ በመርከብ ውክልና ቢያንስ የአምስት ዓመት ልምድ ያላቸው መሆኑ፤ እና

2. ለሚሰጠው አገልግሎት የተዘጋጀ ታሪፍ ያለው መሆኑ፣

**አንቀጽ 17፡- <u>ኢንተርሞዳል ተርሚናል የመሰረተልማት እና የመሳሪያዎች ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>**

ማንኛውም ሰው የኢንተርሞዳል ተርሚናል የመሰረተልማትና የመሳሪያዎች ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተለውን ማሟላት ይኖርበታል፤

1. ከሶስት ሜትር ከፍታ ያላነሰ በሽቦ አጥር ወይም በግንብ የታጠረና ደህንነቱ በተጠበቀ በአጠቃላይ 4 ሄክታር ቦታ ያለው እና ከዚህ ውስጥ 3.5 ሄክታር ቦታ ላይ በአስፋልት ኮንክሪት የተገነባ የባቡር መስመር ያለው ተርሚናል፣
2. ባለ 45 ቶን 1 ሪች ስታከር፣ ባለ 3-10 ቶን 2 ፎርክ ሊፍት፣ ባለ 40 ቶን 2 ተርሚናል ትራክተር ከነተሳቢው እና ባለ 45 ቶን 1 Rail Mounted Gantry በባለቤትነት ወይም ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ 1 ፎርክ ሊፍት እና 2 ተርሚናል ትራክተር ቢያንስ በአራት ዓመት ኪራይ እና ሌሎቹን በባለቤትነት፤
3. እያንዳንዳቸው ቢያንስ በ0.1 ሄክታር ቦታ ላይ የተገነቡ ሶስት መጋዘኖች፣
4. ለተቆጣጣሪ እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሆን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደራጀ ቢሮ፣
5. የጥበቃ ማማ  እና የደህንነት መሳሪያዎች ፣ የነፍስ ወከፍ አደጋ መከላከያ መሳሪያዎች እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የደህንነት የመቆጣጠሪያ ማዕከል ፣
6. አንድ ባለ 2000 ሊትር የእሳት አደጋ ተሽከርካሪ እና ሌሎች የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያዎች፣ በአደጋ ጊዜ መውጫ በር እና መሰብሰቢያ ቦታ፣
7. የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ማዕከል ፣
8. በአንድ ጊዜ ለ10 ከባድ ተሽከርካሪዎች ማቆሚያ የሚሆን በአስፋልት የተገነባ ቦታ ፣

**አንቀጽ 18፡- <u>ኢንተርሞዳል ተርሚናል የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>**

ማንኛውም ሰው የኢንተርሞዳል ተርሚናል የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተለውን ማሟላት ይኖርበታል፤

1. አንድ ከፍተኛ ሥራ መሪ እና ከ14 ያላነሱ ባለሞያዎች ያሉት እና ባለሞያዎቹ በዕቃ አስተላላፊነት፣ በጉምሩክ አስተላላፊነት፣ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት፣ በመርከብ ውክልና ቢያንስ የአምስት የስራ ልምድ ያላቸው መሆኑ፤ እና
2. ለሚሰጠው አገልግሎት የተዘጋጀ ታሪፍ ያለው መሆኑ፣

## ክፍል አራት

## የሎጅስቲክስ ፓርክ ልማት እና የአገልግሎት ብቃት መስፈርቶች

**አንቀጽ 19፡- <u>የሎጅስቲክስ ፓርክ የመሰረተልማት እና የመሳሪያዎች ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>**

ማንኛውም ሰው የሎጅስቲክስ ፓርክ የመሰረተ ልማትና የመሳሪያዎች ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተለውን ማሟላት ይኖርበታል፤

1. ከሶስት ሜትር ከፍታ ያላነሰ በግንብ የታጠረና ደህንነቱ በተጠበቀ በትንሹ 33 ሄክታር አጠቃላይ ቦታ ያለው እና ከዚህ ውስጥ 9 ሄክታር የለማ ሆኖ 3 ሄክታር በአስፋልት ኮንክሪት የተገነባ የኮንቴይነር ተርሚናል ቀሪው በአስፋልት ኮንክሪት ወይም በቀይ አፈር የተነጠፈ የጥቅል ዕቃ እና የተሽከርካሪ ተርሚናሎች ያሉት፣
2. ቢያንስ ባለ 45 ቶን 4 ሪች ስታከር ፣ 1 ብሎዊንግ ማሽን ፣ ባለ 45 ቶን 6 ተርሚናል ትራክተር ከነተሳቢው ፣ ባለ 3- 25 ቶን 15 ፎርክ ሊፍት ፣ ባለ 45 ቶን 2 Rubber Tiered Gantry እና ባለ 40 ቶን 1 ሞባይል ክሬን በባለቤትነት ወይም ፣ ከእነዚህ ውስጥ 2 ሪች ስታከር፣ 3 ተርሚናል ትራክተር፣ 7 ፎርክ ሊፍት ቢያንስ በአራት ዓመት ኪራይ እና ሌሎቹን በባለቤትነት፤
3. በ4 ሄክታር ላይ የተገነቡ ከ3 ያላነሱ መጋዘኖች፣
4. ለተቆጣጣሪ እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቢሮ የሚሆን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደራጀ በ0.5 ሄክታር ላይ የተገነባ ቢሮ፣
5. የወደብ መሳሪያ እና የተሽከርካሪ የጥገና እና የኮንቴይነር እጥበት ማዕከል፣
6. ባለ 5000 ሊትር ሁለት የእሳት አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አንድ አምቡላንስ እንዲሁም በመሳሪያ የተደራጀ የእሳት አደጋ መከላከያ ማዕከል፣
7. የጥበቃ ማማ እና የደህንነት መሳሪያዎች ፣ የነፍስ ወከፍ አደጋ መከላከያ መሳሪያዎች እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የደህንነት የመቆጣጠሪያ ማዕከል እና የዕቃ መፈተሻ ማሽን መትከያ ቦታ፣
8. በሎጅስቲክስ ፓርኩ ውስጥ ለሚያገለግሉ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል የነዳጅ ማደያ፣
9. የምድር ሚዛን፣
10. መካከለኛ ክሊኒክ ፣
11. ምግብ ቤት እና ካፌ፣
12. የተገነባ በአንድ ጊዜ ለ60 ከባድ ተሽከርካሪዎች ማቆሚያ የሚሆን በአስፋልት የተገነባ ቦታ፣

**አንቀጽ 20፡- <u>የሎጅስቲክስ ፓርክ የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>**

ማንኛውም ሰው የሎጅስቲክስ ፓርክ የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተለውን ማሟላት ይኖርበታል፤

1. ሁለት ከፍተኛ ሥራ መሪ እና ከ48 ያላነሱ ባለሞያዎች ያሉት እና ባለሞያዎቹ በዕቃ አስተላላፊነት፣ በጉምሩክ አስተላላፊነት፣ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት፣ በመርከብ ውክልና ቢያንስ የአምስት ልምድ ያላቸው መሆኑ፤ እና
2. ለሚሰጠው አገልግሎት የተዘጋጀ ታሪፍ ያለው መሆኑ፣

## ክፍል አምስት

## የሎጅስቲክስ ሀብ ልማት እና የአገልግሎት ብቃት መስፈርቶች

**አንቀጽ 21 ፡- <u>የሎጅስቲክስ ሀብ የመሰረተልማት እና የመሳሪያዎች ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>**

ማንኛውም ሰው የሎጅስቲክስ ሀብ የመሰረተልማት እና የመሳሪያዎች ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተለውን ማሟላት ይኖርበታል፤

1. ከሶስት ሜትር ከፍታ ያላነሰ በግንብ የታጠረና ደህንነቱ የተጠበቀ በትንሹ አጠቃላይ 80 ሄክታር ቦታ ያለው እና ከዚህ ውስጥ 34 ሄክታር ቦታ በአስፋልት ኮንክሪት የተገነባ የኮንቴይነር ፣ የደረቅ ብትን ጭነት ፣ የጥቅል ዕቃ ፣ የተሽከርካሪ እና የኢንተርሞዳል ተርሚናሎች ያሉት፣
2. ባለ 45 ቶን 10 ሪች ስታከር ፣ 2 ብሎዊንግ ማሽን ፣ ባለ 40 ቶን 10 ተርሚናል ትራክተር ከነተሳቢው ፣ ከ3 — 25 ቶን 44 ፎርክ ሊፍት ፣ ባለ 45 ቶን 2 Rubber Tiered Gantry፣ ባለ 45 ቶን 1 ሞባይል ክሬን እና ባለ 45 ቶን 1 Rail Mounted Gantry በባለቤትነት ወይም ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ 5 ሪች ስታከር፣ 1 ብሎዊንግ ማሽን፣ 5 ተርሚናል ትራክተር፣ 22 ፎርክ ሊፍት ቢያንስ በአራት ዓመት ኪራይ እና ሌሎቹን በባለቤትነት፣
3. በስምንት ሄክታር ላይ የተገነቡ ከአራት ያላነሱ መጋዘኖች እና ቢያንስ ከዚህ ውስጥ አንድ መጋዘን የማቀዝቀዣ መሳሪያ የተገጠመለት፣
4. ለተቆጣጣሪ እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቢሮ የሚሆን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደራጀ በ1 ሄክታር ላይ የተገነባ ቢሮ ያለው፣
5. ለወደብ መሳሪያዎች የጥገና እና የኮንቴይነር እጥበት ማዕከል፣
6. ባለ 5000 ሊትር አራት የእሳት አደጋ ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች የእሳት አደጋ መከላከያ ቁሳቁሶች፣ በአደጋ ጊዜ መውጫ በር እና መሰብሰቢያ ቦታ እንዲሁም አንድ አምቡላንስ፣

7. የጥበቃ ማማ ፣ የደህንነት መሳሪያዎች ፣ የነፍስ ወከፍ አደጋ መከላከያ መሳሪያዎች እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የደህንነት መቆጣጠሪያ ማዕከል፣
8. በሎጅስቲክስ ሀብ ውስጥ ለሚያገለግሉ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል የነዳጅ ማደያ፣
9. የዕቃ መፈተሻ መሳሪያ መትከያ ቦታ፣
10. የምድር ሚዛን፣
11. ጤና ጣቢያ ወይም ከፍተኛ ክሊኒክ፣
12. ምግብ ቤት እና ካፌ፣
13. በአንድ ጊዜ ለ100 ከባድ ተሽከርካሪዎች ማቆሚያ የሚሆን በአስፋልት የተገነባ ቦታ፣
14. የዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪ ማዕከል፣

**አንቀጽ 22፡- <u>የሎጅስቲክስ ሀብ የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>**

ማንኛውም ሰው የሎጅስቲክስ ሀብ የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተለውን ማሟላት ይኖርበታል፤

1. ሁለት ከፍተኛ ሥራ መሪ ፣ 10 መካከለኛ ሥራ መሪ እና ቢያንስ 57 ባለሞያዎች ያሉት እና ባለሞያዎቹ በዕቃ አስተላላፊነት፣ በጉምሩክ አስተላላፊነት፣ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት፣ በመርከብ ውክልና ቢያንስ የአምስት ልምድ ያላቸው መሆኑ፤ እና
2. ለሚሰጠው አገልግሎት የተዘጋጀ ታሪፍ ያለው መሆኑ፣

**አንቀጽ 23፡- <u>ተጨማሪ አገልግሎቶችን ስለመስጠት</u>**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9፣10፣11፣12፣13፣14፣15፣16፣17፣18 የተዘረዘሩት መስፈርቶች መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ የልዩ ተርሚናል አገልግሎት ሰጪ ብቃት ካገኘበት የልዩ ተርሚናል አገልግሎት በተጨማሪ በአባሪ ላይ የተገለጹትን አሟልቶ ሲገኝ ተጨማሪ አገልግሎት መስጠት ይችላል፤

## ክፍል ስድስት

## ግዴታዎች እና ክልከላዎች

**አንቀጽ 24፡- የደረቅ ወደብና ተርሚናል አልሚ እና የአገልግሎት ሰጪ ግዴታዎች**

ማንኛውም የደረቅ ወደብና ተርሚናል አልሚ እና አገልግሎት ሰጪ የሚከተለው ግዴታ አለበት፣

1. የተረከበውን ዕቃ ደህንነት በመጠበቅ ለዕቃው ባለቤት ወይም ለወኪሉ ማስረከብ፤
2. ከመንግስት ተቆጣጣሪ ተቋማት ጋር በተቀናጀ መልኩ መስራት፤
3. የገንዘብ ልውውጦች፣ የሥራ ግንኙነቶችንና ከሥራው ጋር የተያያዙ መረጃዎችና ሰነዶች ማደራጀት፣ መመዝገብ እና እስከ አስር ዓመት ድረስ ይዞ ማቆየት፤
4. ባለስልጣኑ የሚጠይቃቸውን ሰነዶችና መረጃዎችን እንደአስፈላጊነቱ በሚጠየቅበት ጊዜ ማቅረብ ፤
5. በደረቅ ወደብና ተርሚናል ውስጥ በህግ ከተወሰነላቸው የጊዜ ገደብ በላይ የተከማቹ ዕቃዎችን በህግ ለተፈቀደለት አካል ማሳወቅ እና ማስተላለፍ፣
6. ዕቃ በደረቅ ወደብና ተርሚናል ውስጥ እያለ ቢጠፋ እንዲሁም በአገልግሎት ሰጪው ጥፋት ዕቃው ቢጎዳ አግባብ ባለው የህግ መሰረት ለባለዕቃውን ካሳ የመክፈል፣
7. የተረከበውን ዕቃ በደረቅ ወደብና ተርሚናል ውስጥ እያለ ቢጠፋ አስፈላጊውን ቀረጥና ታክስ ለጉምሩክ ኮሚሽን የመክፈል፣
8. የደረቅ ወደብና ተርሚናል አልሚው አገልግሎቱን በራሱ የሚሰጥ ከሆነ የኢንሹራንስ ሽፋን ፣ እንዲሁም አገልግሎቱ በሌላ ወገን የሚሰጥ ከሆነ አገልግሎት ሰጪው የኢንሹራንስ ሽፋን እንዳለው የማረጋገጥ፣
9. በወደብና ተርሚናል ውስጥ በሌላ ወገን ለሚሰጡ አገልግሎቶች ግልጽ የሆነ የአሠራር መዘርጋት እና ውል የመግባት፣

**አንቀጽ 25፡- ክልከላ**

ማንኛውም የወደብና ተርሚናል አልሚ እና አገልግሎት ሰጪ የሚከተሉትን መፈጸም አይፈቀድለትም፣

1. ፍቃዱ የተሠረዘበት ወይም የታገደበት ከሆነ ከደንበኛ ጋር አዲስ አገልግሎት መዋዋል እና አልሚው ከአገልግሎት ሰጪ ጋር ውል መግባት፣

## ክፍል ሰባት

## የብቃት ማረጋገጫ ዕድሳት፣ ዕገዳና ስረዛ

**አንቀጽ 26፡- የብቃት ማረጋገጫ እድሳት ስለማስፈለጉ**

በዚህ መመሪያ ለተጠቀሱት የብቃት ማረጋገጫ አይነቶች በሙሉ በሚከተለው ሁኔታ እድሳት የሚሰጥ ይሆናል

1. የብቃት ማረጋገጫው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በየበጀት ዓመቱ ባሉት የመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት ውስጥ ለባለስልጣኑ እያቀረበ ማሳደስ፤
2. የብቃት ማረጋገጫውን ለማሳደስ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወስነውን የአገልግሎት ክፍያ መክፈል፤
3. የብቃት ማረጋገጫው ለእድሳት ከተቀመጠው የሶስት ወር ጊዜ በኋላ ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወስነውን የቅጣት ክፍያ በመክፈል ማሳደስ፤
4. አገልግሎት ሰጪው በመስፈርቱ መሰረት አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ፤

**አንቀጽ 27፦- <u>ማስጠንቀቂያ ስለመስጠት</u>**

ማንኛውም የደረቅ ወደብና ተርሚናል አልሚና አገልግሎት ሰጪ ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከዛ በላይ ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ በባለስልጣኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፣

1. ባለስልጣኑ በሚያስቀምጠው ስታንዳርድ መሰረት ቢያንስ ለሁለት ተከታታይ ጊዜ ሪፖርት ያላቀረበ እንደሆነ፣
2. በመስክ ምልከታ ወቅት የመሰረተልማት፣ የመሳሪያ እና የሰው ሃይል ከዝቅተኛ መስፈርት በታች አሰማርቶ መገኘቱ ሲረጋገጥ

**አንቀጽ 28፦- <u>የብቃት ማረጋገጫ ስለማገድ</u>**

የደረቅ ወደብና ተርሚናል አልሚ እና አገልግሎት ሰጪ ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከዛ በላይ ጥፋት መፈጸሙ ከተረጋገጠ ጉድለቱን እስኪያስተካክል ድረስ የብቃት ማረጋገጫው በባለስልጣኑ ሊታገድበት ይችላል

1. የወደብና ተርሚናል አልሚው ያለ በቂ ምክንያት በዚህ ደንብ አንቀጽ 26 (1) እና (3) መሠረት ፈቃዱን በአራት ወር ጊዜ ያላሳደሰ እንደሆነ፤
2. ባለስልጣኑ በሚያስቀምጠው መስፈርት መሰረት ቢያንስ ለሶስት ተከታታይ ጊዜ ሪፖርት ያላቀረበ እንደሆነ፣
3. በዚህ መመሪያ ላይ ከተገለጸው የባለሞያ ብዛት በታች ሲያሰራ የተገኘ እንደሆነ፣

**አንቀጽ 29፦- <u>የብቃት ማረጋገጫ ስለመሰረዝ</u>**

የደረቅ ወደብና ተርሚናል አልሚ እና አገልግሎት ሰጪ ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከዛ በላይ ጥፋት መፈጸሙ ከተረጋገጠ የብቃት ማረጋገጫው በባለስልጣኑ ሊሰረዝ ይችላል

1. የብቃት ማረጋገጫው የተገኘው በማታለል ወይም በማጭበርበር ወይም የሀሰት ማስረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ መሆኑ ሲረጋገጥ፣
2. ይህን መመሪያ የሚጻረር ድርጊት መፈጸሙ የተረጋገጠ እንደሆነ፣

3. የደረቅ ወደብና ተርሚናል አልሚ እና አገልግሎት ሰጪ ከመታገዱ በፊት ከተቀበላቸው የሥራ ውሎች ውጪ በታገደበት ወቅት አገልግሎት መስጠቱ የተረጋገጠ እንደሆነ፣

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 30፡- የሚኒስቴሩ ስልጣንና ተግባር**

የዚህን መመሪያ አፈጻጸም በተመለከተ ሚኒስቴሩ የሚከተለው ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል፣

1. የዚህን መመሪያ አፈጻጸም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
2. አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ጊዜ መመሪያውን ሊያሻሽል ይችላል፣
3. በደረቅ ወደብና ተርሚናል ኢንቨስትመንት፣ አገልግሎት አቅርቦት እና አገልግሎት ተጠቃሚዎች በተመለከተ የሚነሱ ማናቸውንም ቅሬታዎች የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣

**አንቀጽ 31፡- የባለስልጣኑ ስልጣንና ተግባር**

የዚህን መመሪያ አፈጻጸም በተመለከተ ባለሥልጣኑ የሚከተለው ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል፣

1. የደረቅ ወደብ እና ተርሚናል ልማትና አገልግሎት ላይ የተሰማሩ ባለሃብቶች ያሉባቸው ችግሮች በጥናት በመለየት መፍትሄ ሃሳቦችን ለሚኒስቴር ያቀርባል ያስወስናል ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፤
2. ባለስልጣኑ የደረቅ ወደብ እና ተርሚናል አልሚ እና አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሲያድስ የብቃት ማረጋገጫው ሲሰጥ የነበረው መሰረተ ልማት፣ መሳሪያ እና የሰው ሃይል መኖሩን ያረጋግጣል፣
3. የልዩ ተርሚናል የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ አገልግሎት ሰጪ ተጨማሪ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችል የመሳሪያ እና የሰው ሃይል ማሟላቱን በማረጋገጥ እንዲሰራ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤
4. በመስክ ቁጥጥር የተገኙ ግብረ መልሶችን በማዘጋጀት ለአልሚው እና ለአገልግሎት ሰጪ ያሳውቃል፣
5. የደረቅ ወደብና ተርሚናል አልሚዎች ሆነ አገልግሎት ሰጪዎች የሚሰጡትን አገልግሎት የተመለከተ ሪፖርት የሚያቀርቡበት ስርዓት ይዘረጋል፤ ሪፖርቱን ተቀብሎ ይተነትናል፤አስፈላጊውን ማሻሻያ ያደርጋል፤ለሚመለከተው የበላይ አካልም ያሳውቃል፤
6. የብቃት ማረጋገጫ የተሠጣቸዉ፣ የታገደባቸው እና የተሠረዘባቸው አልሚና አገልግሎት ሰጪዎች ዝርዝር ወቅታዊ መረጃ አዘጋጅቶ ለንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና ለብሔራዊ ባንክ ያሳውቃል እንዲሁም ለአገልግሎት ፈላጊ ይፋ ያደርጋል፣ ፣
7. ባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የሚታደስበትን ዝርዝር መስፈርት ያዘጋጃል፤
8. የአገልግሎት ታሪፍ ያጸድቃል፤

**አንቀጽ 32፡- <u>የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነትና የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

1. የንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸዉ ሕጎች በዚህ መመሪያ ላይ እንደ አግባቡ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፣
2. የነባር ደረቅ ወደብና ተርሚናል ልማትና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሁለት ዓመት ውስጥ በዚህ መመሪያ መስፈርት መሰረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከባለሰልጣኑ መውሰድ ይኖርባቸዋል፣

**አንቀጽ 33፡- <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር

# አባሪ

| | ኮንቴይነር ተርሚናል | ኢንተርሞዳል ተርሚናል |
|---|---|---|
| መስጠት የሚችሉ ተጨማሪ አገልግሎቶች | ኢተርሞዳል ተርሚናል (ከባቡር መስመር ጋር የተያያዘ ከሆነ) ፣ የደረቅ ብትን ጭነት ተርሚናል፣ የጥቅል ዕቃ ተርሚናል፣ የተሽከርካሪ ተርሚናል | ኮንቴይነር ተርሚናል፣ የደረቅ ብትን ጭነት ተርሚናል፣ የጥቅል ዕቃ ተርሚናል፣ የተሽከርካሪ ተርሚናል |
| መሟላት ያለባቸው ተጨማሪ መሳሪያዎች | በአንቀጽ 8(ለ) ቁጥር 2 ስር ከተዘረዘሩት መሳሪያዎች በተጨማሪ<br>ቢያንስ 1 ባለ 45 ቶን ሞባይል ክሬን፣ 1 ባለ 3 - 25 ቶን ፎርክሊፍት ፣ 0.01 ሄክታር የተሽከርካሪ መጋዘን እና 0.1 ሄክታር መጋዘን ለጥቅል ጭነት ዕቃ፤<br>የደረቅ ብትን ጭነት ተርሚናል አገልግሎት ለመስጠት፡- 1 ባጊንግ ማሽን ፣ ባለ5 ቶን ሎደር፣ 0.5 ሄክታር ለደረቅ ብትን ጭነት መጋዘን<br>የኢንተርሞዳል ተርሚናል አገልግሎት ለመስጠት፡- ባለ 45 ቶን RMG | በአንቀጽ 12(ለ) ቁጥር 2 ስር ከተዘረዘሩት መሳሪያዎች በተጨማሪ<br>ቢያንስ 1 ባለ 45 ቶን ሞባይል ክሬን፣ 1 ባለ 3 - 25 ቶን ፎርክሊፍት ፣ 0.01 ሄክታር የተሽከርካሪ መጋዘን፣ ለጥቅል ጭነት ዕቃ 0.05 ሄክታር መጋዘን እና 0.1 ሄክታር ለኮንቴይነር ተርሚናል መጋዘን ፤<br>የደረቅ ብትን ጭነት ተርሚናል አገልግሎት ለመስጠት፡- 1 ባጊንግ ማሽን ፣ 0.5 ሄክታር ለደረቅ ብትን ጭነት መጋዘን 0.3 ሄክታር፣ |
| መሟላት የሚገባቸው ተጨማሪ የሰው ሃይል | አንቀጽ 8(ሐ) ቁጥር 1 ስር ከተዘረዘሩት ባለሞያዎች በተጨማሪ 10 ባለሞያዎች እንዲሁም ለኢንተርሞዳል ተርሚናል ተጨማሪ 6 ባለሞያዎች እና ለደረቅ ብትን ጭነት ተርሚናል 8 ባለሞያዎች | አንቀጽ 12(ሐ) ቁጥር 1 ስር ስር ከተዘረዘሩት ባለሞያዎች በተጨማሪ 18 ባለሞያዎች እና ለደረቅ ብትን ጭነት ተርሚናል 8 ተጨማሪ ባለሞያዎች |

| | የተሸከርካሪ ተርሚናል | የጥቅል ዕቃ ተርሚናል | የደረቅ ብትን ጭነት ተርሚናል |
|---|---|---|---|
| መሰጠት የሚችሉ ተጨማሪ አገልግሎቶች | የጥቅል ዕቃ ተርሚናል | የተሽከርካሪ እና የደረቅ ብትን ጭነት ተርሚናል | የተሽከርካሪ እና የጥቅል ዕቃ ተርሚናል |
| መሟላት ያለባቸው ተጨማሪ መሳሪያዎች | በአንቀጽ 12(ለ) ቁጥር 2 ስር ከተዘረዘሩት መሳሪያዎች በተጨማሪ ቢያንስ 1 ባለ 45 ቶን ሞባይል ክሬን ፣ 2 ባለ 3-25 ቶን ፎርክሊፍት እንዲሁም 0.1 ሄክታር መጋዘን | በአንቀጽ 10(ለ) ቁጥር 2 ስር ከተዘረዘሩት መሳሪያዎች በተጨማሪ ቢያንስ ባለ 3 ቶን 1 ፎርክ ሊፍት፣ 0.01 ሄክታር የተሽከርካሪ መጋዘን የደረቅ ብትን ጭነት አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ባለ5 ቶን 1 ሎደር ፣0.3 ሄክታር መጋዘን እና 1 ባጊንግ ማሽን ፣ | በአንቀጽ 9(ለ) ቁጥር 2 ስር ከተዘረዘሩት መሳሪያዎች በተጨማሪ 1 ባለ 45 ቶን ሞባይል ክሬን፣ 2 ፎርክሊፍት ፣ 0.01 ሄክታር ለተሽከርካሪ እና 0.1 ሄክታር ለጥቅል ዕቃ መጋዘን |
| መሟላት የሚገባቸው ተጨማሪ የሰው ሃይል | በአንቀጽ(ሐ) ቁጥር 1 ስር ከተዘረዘሩት ባለሞያዎች በተጨማሪ 6 ባለሞያዎች | በአንቀጽ10(ሐ) ቁጥር 1 ስር ከተዘረዘሩት ባለሞያዎች በተጨማሪ ለተሽከርካሪ ተርሚናል በተጨማሪ 5 ባለሞያወች እና ለደረቅ ብትን ጭነት 8 ባለሞያዎች | በአንቀጽ 9(ሐ) ቁጥር 1 ስር ከተዘረዘሩት ባለሞያዎች በተጨማሪ 10 ባለሞያዎች |